# የአዲስ አበባ ከተማ የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

## 1. ረቂቅ መመሪያው ያስፈለገበት ምክንያት

እንደሚታወቀው የማዕድን ሥራዎችን ለማከናወን መሰረታዊ የህግ ማዕቀፎች የማዕድን ሥራዎች አዋጅ 678/2002 እና የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 ሲሆን ባጠቃላይ በማዕድን አዋጅና ደንብ ላይ እንደተገለጸው

- የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት የመንግስትና የህዝብ በመሆኑና የማይታደስ ሃብት ስለሆነ ሃብቱን ለመጠበቅ እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ለማሳደግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ተገልጋዮችን ሊያረካ በሚችል መልኩ ቀልጣፋ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲኖረው ለማድረግ፣
- የከተማውን የኮንስትራክሽን ማዕድን ክምችት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ ጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃ ለማደራጀት፤
- ተገልጋዮች መረጃውን ብቃት ባለው መንገድ እንዲጠቀሙና የአመራረት ሥራውን ዘመናዊ ለማድረግ እና አካባቢን ያገናዘበና ከስነምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው እና ለከተማው ሁለንተናዊ ልማት የሚውል የኮንስትራክሽን ማዕድን ግብዓት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት መሰረታዊ ምክንያቶች በተጨማሪ

- የማዕድን አዋጅና ደንቡ የሚያጠቃልለው በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ከከበሩ ማዕድናት ጀምሮ እስከ ኮንስትራክሽን ማዕድን ድረስ ያሉትን ሲሆን በአብዛኛው ጠቅለል ባሉ ጉዳዮች ላይ የተደነገገ በመሆኑና በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኘው የኮንስትራክሽን ማዕድናት ብቻ በመሆናቸው በአፈጻጸም ሂደት ላይ ማብራሪያ የሚያስፈጋቸውና በከተማ ውስጥ የሚካሄድ የማዕድን ማምረት ስራ በመሆኑ  አካባባውን ያገናዘብ ከአዋጁና ደንቡ ጋር የሚጣጣም  ዝርዝር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ፡፡
- በተጨማሪም ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረው መመሪያ አሰራሩን ተከትሎ ባለመጽደቁና ቁጥር ስላልተሰጠው ህጋዊ መመሪያ አድርጎ መጠቀም እንደማይቻል ስለታመነበት እና ወቅቱን ያገናዘበ የአሰራር ስርዓቶችና ከተማውን የሚመጥን የፈቃድ አስጣጥ አሰራር  ስለተዘርጋ ረቂቅ መመሪያውን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል

2. የረቂቅ መመሪያው ማብራሪያ

ረቂቅ መመሪያው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ለልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች በቀጥታ በግብአትነት እየዋለ የሚገኘውን በከተማዋ ክልል የሚገኙ ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በማጥናት የማዕድን ማምረት ፈቃድ መስጠትና ማስተዳደር ፤ ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም የከተማዋ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ ፤ከዘርፉ ከሮያሊቲና ከሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች የሚሰበሰብ ልዩ ልዩ ገቢ ለመሰብሰብ ቀልጣፋና ውጤታማ ስርዓት ለመዘርጋት፤በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በፈቃድ አሰጣጥ ክትትልና ቁጥጥር በማምረትና በገቢ አሰባሰቡ ፣በመረጃ አያያዝና አቀራረብ፣ ያለውን ኃላፊነት ተጠያቂነት ሊያሳይ የሚችል የአሰራር ስርዓትን ያካተተ ነው ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ አፈጻጸም መመሪያ በሚል የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ በአጠቃላይ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን

በክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች በሚለው ስር ስያሜውን፣ ትርጓሜዎችንና የተፈጻሚነት ወሰኑን እንዲሁም የመምሪያውን አላማ ያካተተ ነው ።

በክፍል ሁለት የማዕድን ፈቃድ በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮች የተካተቱበት ሲሆን ማንኛውም ሰው ያለፈቃድ የኮንስትራክስን ማዕድን ማምረት እንደማይችል እና በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በቀር ፈቃድ ስለማይሰጥባቸው ቦታዎች ዝርዝ ያስቀምጣል ። እንዲሁም በከተማዋ ክልል የሚገኙ የኮንስትራክሽን ማዕድን አይነቶችና የሚሰጡ የፈቃድ አይነቶች እንዲሁም ማንኛውም ፈቃድ የሚጠይቅ አካል ሊያሟላቸው የሚገቡ መረጃዎችን ግልጽ በሆነ መንገድ ያብራራል ።

በክፍል ሶስት  የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና የክ/ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት ስለሚኖራቸው ተግባርና ሃላፊነት ፤ የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ የሚሰጥበትን የውል ዘመን፤ አዲስ እና ነባር ፈቃዶች ስለሚሰጡበት አሰራር፤ እንዲሁም በአርሶ አደርና በማህበር ለተደራጁ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ መሟላት ስላለባቸው መረጃዎች፣ የማስፋፋያ ጥያቄ ሲቀርብ ሊሟሉ የሚገባቸው መረጃዎች፣ ከስራው ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ መሳሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ፤ ፈቃድ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች፤ እንዲሁም ማዕድኑ ከተመረተ በኂላ ለመንግስት ስለሚከፈል የሮያልቲ ክፍያ እና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያዎች በማዕድን አዋጅ ደንብና ሌሎች የክፍያ ደንቦች መሰረት መከፈል እንዳለባቸው ተደንግጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ ክፍል ለመንግስታዊ ፕሮጀክቶች የኮንስትራክሽን ማዕድን ፈቃድ ለሚጠይቁ የሚስተናገዱበት አግባብ እና ፈቃድ ስለሚስረዝባቸው ምክንያቶች፣ ስለጥፋቶችና ሊወሰዱ ስለሚገባቸ እርምጃዎች በዚሁ ክፍል ለማብራራት ተሞክሯል ፡፡

በክፍል አራት የተዘረዘሩት ዋና ዋና ድንጋጌዎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የሚያካትት ሲሆን መመሪያውን የመተግበር ግዴታዎች፣ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች እና መመሪያያው የሚጸናበት ጊዜ በማካተት የመመሪያው የመጨረሻ ክፍል በመሆን ተጠቃሏል ፡፡

ባጠቃላይ ይህ መመሪያ ጽድቆ ወደ ስራ ሲገባ በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ሲሆን የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል

1. የአዲስ አበበአ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በአዋጅ 84/2016 ከተሰጡት ተግባርና ሃላፊነቶች አንዱ የሆነውን በከተማዋ ክልል የሚገኙ የኮንስትራክሽን ማዕድናት በህጋዊ መንገድ ተምርተው ለከተማዋ ልማት እንዲውሉ ያስችላል
2. ህገወጥ የማእድን ሥራዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ያስችላል
3. በማዕከልና በክ/ከተማ የሚተገበሩ ዋና ዋና ተግባራትና ሃላፊነቶችን በመለየት የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል

4. በባለሃብቱ የሚቀርቡ ወርሃዊ ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ የክትትልና ድጋፍ ሥርዐትን በመዘርጋት ከዘርፉ የሚሰበሰበውን የመንግስት ገቢ በአግባቡ ለመሰብሰብ ያስችላል የእያንዳንዱ በስራው ላይ የሚሳተፍ ከሃላፊ ጀምሮ እስከባለሙያ ድረስ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል ።